# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## “ከጅብ ጅማት የተሠራ ክራር ቅኝቱ እንብላው ነው” !

በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው የሕወሓት/ኢሕአዴግ ሽብርተኛ አገዛዝ ሥልጣን ከጨበጠበት ጊዜ ጀምሮ የሚደርስበትን ያልተቋረጠ ተቃውሞ ለማፈንም ሆነ የተቃዋሚውን የለውጥ አጀንዳ ለማውገርገር ሲያሻው “በአገር-ክህደት”፣ ሲፈልግም እራሱ የማያከብረውንና የማይገዛበትን 'ሕገ-መንግሥት' በማጣቀስ “ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓትን በሕገ-ወጥ መንገድ ለማስወገድ” በሚልና በሌሎችም መያዣ መጨበጫ በሌላቸውና አልፎ አልፎም በተቃርኖ በታጀቡ ክሶች በተቃዋሚው ወገን በግልጽ የተሰለፉ ክፍሎችንም ይሁን ይቃወሙኝ ይሆናል ብሎ የሚያስባቸውን ንፁኃን ዜጎች ሲያምስ፣ ሲያንከራትት፣ ለስደት፣ ለእስር፣ ለእንግልትና ለሞት ሲዳርግ መታየቱ አዲስ ክስተት አይደለም፡፡
በቅርቡም በተለይ የ“ግንቦት ሰባት” አባላት ናቸው በሚል ጥርጣሬ የሠራዊቱን አባላትና ሲቪሎችን እንዲሁም በድርጅቱ የተሰለፉ ግለሰቦችን ቤተሰቦችና የዝምድና ሐረግ እየተሳበ የሰማንያ ዓመት አረጋዊ ሳይቀሩ ለእስር መዳረጋቸውን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት አጥብቆ ያወግዛል፡፡ እነኝኽ ዜጎች በአስቸኳይ እንዲፈቱም ይጠይቃል፡፡

የግንቦት ዘጠና-ሰባት አንፀባራቂ የሕዝብ ድሎች ከተቀለበሱ ወዲህ በአገራችን ያለው የፖለቲካ ምኅዳር ከጊዜ ወደጊዜ ይበልጥ እየጠበበ ከናካቴው በአገሪቱ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ አንድ ድርጅት (ሕወሓት/ኢሕአዴግ) ብቻ እንዲኖር ሁኔታዎች እየተመቻቹ መገኘታቸው ግልጽ ነው፡፡ ተቃዋሚው እሳካሁን ባለው ይዞታ ከቀጠለ አበው “ከጅብ ጅማት የተሠራ ክራር ቅኝቱ እንብላው ነው” እንዲሉ፣ ይኸ ከዴሞክራሲና ከሕዝብ ክብር ጋር ትውውቅ የራቀው አገዛዝ በሰበብ አስባቡ በተቃዋሚ ድርጅቶችና በደጋፊዎቻቸው እንዲሁም እነሱን ሊደግፉ ይችሉ ይሆናል ብሎ በጠረጠራቸው ዜጎች ላይ የሚወስዳቸውን ጭፍን የአፈና እርምጃዎች እንዳሻው ከመውሰድ ለመገታት ድርጅታዊ ባኅሪው አያስችለውም፡፡ የሕዝብን ይሁንታና አመኔታ ያጣና ሥልጣኑን በጥሬ ጉልበት ብቻ ለማስጠበቅ የሚጥር አገዛዝ ለሕዝብና ለአገር ብሶትና ደኅንነት ጭንቀት የለውም፡፡

አሁንም ሆነ ምን ጊዜም ኢትዮጵያውያን በአጠቃላይና በተለይም በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፉ ሁሉ አጥብቀው ሊያስቡበትና ተግባራዊ ምላሽ በአፋጣኝ ሊሰጡበት የሚገባው ቁም ነገር የአቶ መለስ አገዛዝ በየጊዜው ይኸን የመሰለ ግፍ በዜጎቻችን ላይ ከመፈጸምም ሆነ የአገርን አንጡራ መሬት ለባዕድ አሳልፎ ከመስጠት አድራጎቶች ሊገታ የሚችለው በመተክል ላይ በተመሠረተ የትግል አንድነት ብቻ መሆኑን ነው፡፡ ይኸ እስካልሆነ ድረስ የተናጠል መርዶ ተቀባይና የሰለባ ተራ ጠባቂ ከመሆንና አገራችንንም ወደ ባሰ አዘቅት ከመኳዝ ማዳን እንደማይቻል ሊታወቅ ይገባል፡፡ በተለይ አገዛዙ ከምርጫ ዘጠና-ሰባት ማግሥት ጀምሮ ደፋ-ቀና ሲልበት የቆየውና አንድ ዓመት ያኽል የቀረው “ምርጫ ሁለት-

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73796
Washington DC 20056-3796, U.S.A
ስልክ ቁ./Tel. 202 361 7162

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
ስልክ Tel/Fax 31 70 394 6132

**ሽሕ-ሁለት" እየተቃረበ በመጣ ቁጥር በረቂቅ ደረጃ ያዘጋጀውን "ፀረ-ሽብርተኝነት" አዋጅ ተግባራዊ ከማድረግ ወደ-ኋላ እንደማይልና አፈናው በየፈርጁ የበለጠ በከፋ መልኩ እንደሚቀጥል ሊጠበቅ ይገባል።**

**ምንም ዓይነት በጎ ፈቃድና ቀና ምኞት ቢኖርም እንኳ በተናጠል ድርጅት በየፌናው የሚደረግ የተበተነ አካሄድን መከተል ለአገርና ለወገን የሚበጅ አዎንታዊ ውጤት አለማምጣት ብቻ ሣይሆን አገዛዙ በሥልጣን ለመቆየት የሚፈልገውን ሰበብ ማመቻቸት እንደሚሆን ይገነዘቧል። ስለሆነም ኢዴኃኅ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፈው አገር-ወዳድና ዴሞክራት ሁሉ የጉዳዩን አሳሳቢነት ከልብ ተገንዝቦ፣ ከድርጅት በላይ አገርንና ሕዝብን በማስቀደም ለጋራ የትግል ጉዞው አፋጣኝ <u>ተግባራዊ ምላሽ</u> እንዲሰጠው ጥሪውን በድጋሜ ያቀርባል።**

**በግፍ የታሰሩ ሁሉ ይፈቱ!**
**አስተማማኝ ድል በተባበረ የሕዝብ ትግል!!**
**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

**የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)**

**ሚያዝያ ፳፭ ቀን ፪ ሺህ ፩ ዓ/ም** (May 3, 2009)

**ዋና መሥሪያ ቤት** (Main Office)
**ፖ.ሣ.ቁ.**/P.O.Box 73796
Washington DC 20056-3796, U.S.A
**ስልክ ቁ.**/Tel. 202 361 7162

**አውሮጳ** (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
**ስልክ** Tel/Fax 31 70 394 6132